# የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና የሚገቡ ተጠቃሚዎች መመልመያ መመሪያ ቁጥር-1058/2017ዓ/ም

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 ፣ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 ፣አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

*ይህ መመሪያ "**የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና የሚገቡ ተጠቃሚዎች መመልመያ መመሪያ ቁጥር-1058/2017ዓ/ም** " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡*

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፤

1) " አዋጅ " ማለት የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 ማለት ነው፡፡
2) " ተጠቃሚዎች " ማለት የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በአዋጁ እንቀጽ 4 የተጠቀሱት ሰዎች ናቸው፡፡
3) " የምስክር ወረቀት " ማለት በወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን እንዲችል በሚኒስቴሩ የሚሰጥ የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት

4) “ የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ” ማለት የማስፋፊያና የማበረታቻ ተግባራትን የሚያከናውን እና በዚህ መመሪያ መሠረት የምስክር ወረቀት የመስጠት ተግባራትን የሚያከናውን በሚኒስቴሩ ስር የተዋቀረ የሥራ ክፍል ነው፡፡

5) “ ሚኒስቴር “ ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፡፡

6) በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት በወጪ የንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ በሆነ ወይም በሚሆን ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

4. <u>የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚኒስቴሩ ማመልከት የሚችሉ ሰዎች፤</u>

   1) አምራች ላኪዎች፤
   2) ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፤ እና
   3) ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች

   ብቻ ናቸው፡፡

5. <u>የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤</u>

   1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተጠቀሱት ሰዎች የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው፣
   2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ፤

      ሀ) አመልካቹ አምራች ላኪ ከሆነ ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን ቅጽ አንድ (ሀ)፤

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት

ለ) አመልካቹ ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ከሆነ ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን ቅጽ አንድ (ለ)፤

ሐ) አመልካቹ ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ከሆነ ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን ቅጽ አንድ (ሐ)፣

መ) የድርጅቱን አጠቃላይ መግለጫ ቅጽ ሁለት "ሀ "፣.

3) ለበጀት ዓመቱ የታደሰ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የንግድ ፈቃድ እና

4) የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት ጉርድ ፎቶግራፍ፣

ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

6. **በዱቤ ወይም በፍራንኮ ቫሉታ ጥሬ ዕቃን ወደ ሀገር ያስገባ አመልካች የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወቀረት ለማግኘት መሟላት ስላለበት ቅድመ ሁኔታዎች፤**

ማንኛውም አምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪ ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢ የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወቀረት ለማግኘት፣

ሀ) በዱቤ ወይም በፍራንኮ ቫሉታ ወደ ሀገር ባስገባው ጥሬ ዕቃ የተመረተውን ምርት በውጭ ሀገር ገዢ መኖሩን የሚያረጋግጥ ከገዢው የተላከ የግዢ ትዕዛዝ ወይም አመልካቹ ከገዢው ጋር ያደረገው የውል ስምምነት፣ ወይም

ለ) አመልካቹ ጥሬ ዕቃው ከተባባሪ የውጭ ኩባንያ (*affiliate foreign company*) የተላከለት መሆኑን የሚገጽ

ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

7. **የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከት የሚችሉ ሰዎች፤**

የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ የሚችሉት፣

1) የቮውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ያልሆኑ፤ እና

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት

2) ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ

ብቻ ናቸው።

8. **የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤**

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተጠቀሱት ሰዎች የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን ቅጽ አንድ "መ" መሠረት ሞልቶ በፊርማውና በድርጅቱ ማኅተም አረጋግጦ ማቅረብ ይኖርበታል።
3) አመልካቹ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቃው ፋብሪካ ያለው ስለመሆኑ ከኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ለሚኒስቴሩ የተጻፈ የማረጋገጫ ደብዳቤ፣
4) ለበጀት ዓመቱ የታደሰ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የንግድ ፈቃድ እና
5) የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት ጉርድ ፎቶግራፍ፣

ማቅረብ ይኖርበታል።

## ክፍል አራት

## የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ስለማግኘት

9. **የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከት የሚችሉ ሰዎች፤**

የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ የሚችሉት፣

1) የቮውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ያልሆኑ፤ እና

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት Ministry Of Industry Archives

2) ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ ለሚቀርብ ምርት ከቀረጥ ነጻ ጥሬ ዕቃዎችን የሚያስገቡ፣ እና

3) ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ

ብቻ ናቸው፡፡

10. **የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤**

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 የተጠቀሱት ሰዎች የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን ቅጽ አንድ "መ" መሠረት ሞልቶ በፊርማውና በድርጅቱ ማኅተም አረጋግጦ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3) አመልካቹ የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቃው የማምረቻ መጋዘን ያለው ስለመሆኑ ከኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ለሚኒስቴሩ የተጻፈ የማረጋገጫ ደብዳቤ፣

4) ለበጀት ዓመቱ የታደሰ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የንግድ ፈቃድ እና

5) የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት ስድስት ወር ያላለፈው አንድ ጉርድ ፎቶግራፍ፣

ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አምስት

## የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ስለማግኘት

11. **የቦንድድ ግባዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከት የሚችሉ ሰዎች፤**

የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ የሚችሉት ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ ለሚቀርብ ምርት ከቀረጥ ነጻ ጥሬ ዕቃዎችን የሚያስገቡ አቅራቢዎች ብቻ ናቸው፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry Archives
መዝገብ ቤት

12. <u>የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 የተጠቀሱት ሰዎች የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ፤

ሀ) ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን ቅጽ አንድ "ሠ" መሠረት ሞልቶ በፊርማውና በድርጅቱ ማኅተም አረጋግጦ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3) አመልካቹ የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቃው መጋዘን ያለው ስለመሆኑ ከኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ለሚኒስቴሩ የተጻፈ የማረጋገጫ ደብዳቤ፣

4) ለበጀት ዓመቱ የታደሰ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የንግድ ፈቃድ እና

5) የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት ስድስት ወር ያላለፈው ሁለት ጉርድ ፎቶግራፍ፣

ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

<u>ክፍል ስድስት</u>

<u>የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚዎች ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና እንዲገቡ ስለመመልመል</u>

13. <u>የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚዎች ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና እንዲገቡ የመመልመያ መስፈርት</u>

ማንኛውም ሰው የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ በመሆን ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና ለመግባት የሚከተሉትን መስፈርቶችን ሚሟላት አለበት፤

1) ግልፅና አሳማኝ የሥራ ዕድል ፈጠራ ዕቅድ ፣

2) ከሌሎች የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት አቅርቦትና ትስስር ያለው መሆኑን ግልጽ ማስረጃ ማቅረብ፤

3) የወጪ ንግድ ወይም መንግሥት በለያቸው ስትራቴጂክ ተኪ ምርቶችን በማምረት ዘርፍ ላይ የሚሰማራ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ፤

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Industry Archives መዝገብ ቤት

4) ዘላቂነት ያለው የፋይናንስ አቅም፣ ምንጭና ታሪክ፤

5) ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል የሠራተኞችን ብቃት ማሳደጊያ የሥልጠና መርሃ-ግብር ማቅረብ፣

6) ከሚመለከታቸው አካላት የአካባቢ ጥበቃ መስፈርቶችን ማሟሉቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ፡፡

## 14. የመመልመያ ነጥብ አሰጣጥ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልተው ማመልከቻ ካቀረቡ የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ አመልካቾች መካከል ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና የሚገባውን አመልካች የሚመረጠው ወይም የሚወሰነው የምስክር ወጪ ሰጪ አካል በሚያቀርበው ሙያዊ የውሳኔ ሐሳብ መነሻ በሚኒስቴሩ በሚሰጥ ውሳኔ መሠረት ይሆናል፡፡

2) የምስክር ወጪ ሰጪ አካል የሚያቀርበው ሙያዊ የውሳኔ ሐሳብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተጠቀሱት መስፈርቶች የተሻለ ውጤት ያመጣውን አመልካች በመለየት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡

## 15. ማመልከቻ ስለማቅረብ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 የተጠቀሱት ሰዎች የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ አመልካቾች ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና ለመግባት ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው፣

2) ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘው ቅጽ አራት ሞልቶ እና ቅጹ የሚጠይቀውን ሰነዶችን በማያያዝ በፊርማውና በድርጅቱ ማኅተም አረጋግጦ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ሰባት

# ስለምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ተግባራት እና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

## 16. የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ኃላፊነት

የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል የሚሰጠው የምስክር ወረቀት በዚህ መመሪያ መሠረት ስለመሰጠቱ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት

## 17. የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ተግባራት

1) ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣
2) በዚህ መመሪያ አፈጻጸም ስላጋጠሙ ተግዳሮቶች፣ ስለመስፈርቶች ክለሳ እና ሌሎች መመሪያውን ለማሻሻል የሚረዱ ሐሳቦችን በማዳበር የውሳኔ ሐሳቡን ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣
3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሙያዊ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፣
4) ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚረዱ መረጃዎችን ሁሉ አደራጅቶ ይይዛል፣
5) ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚረዱ ቅጾችን ያዘጋጃል ወይም የተዘጋጁትን ያሻሽላል::
6) የተሰጡ የምስክር ወረቀቶች በሚኒስቴሩ ድረ ገጽ እንዲጫን ያደርጋል::

## 18. በተጠቃሚዎች የቀረቡ የሰነድ መረጃዎች ትክክለኛነትን ስለማረጋገጥ

1) የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀት ለማግኘት ያቀረቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት ያረጋግጣል ወይም በሚመለከተው አካል እንዲረጋገጥ ማድረግ ይችላል፣
2) የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ተጠቃሚው ባቀረበው መረጃ ከተስተናገደ በኋላ አቅርቦ የነበረው መረጃ ሐሰተኛ ሆኖ ከተገኘ በተጠቃሚው ላይ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ሊወስድ ወይም እንዲወሰድ ማድረግ አለበት::

## 19. የምስክር ወረቀት ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ

1) የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ማመልከቻ ሲቀርብለት በዚህ መመሪያ የተመለከቱት መስፈርቶች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ ሦስት መሠረት ለተጠቃሚው የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት
Ministry Of Industry Archives

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተሟልቶ ለቀረበ ማመልከቻ የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ማመልከቻው በቀረበለት ቢበዛ በአምስት ቀናት ውስጥ የምስክር ወረቀቱን ለተጠቃሚው መስጠት አለበት፡፡

3) ተጠቃሚው ያቀረበው ማመልከቻና ሰነዶች በዚህ መመሪያ መሠረት ተሟልቶ ባለመቅረቡ ወይም የተሳሳተ ወይም ሐሰተኛ በመሆኑ የተነሳ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ሲያረጋግጥ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለተጠቃሚው በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 20. የምስክር ወረቀት ይዘት

የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ለተጠቃሚው የሚሰጠው የምስክር ወረቀት ፤

ሀ) የምስክር ወረቀቱ ባለቤት ድርጅት ሥም፣

ለ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበትን ቀን፣

ሐ) የምስክር ወረቀቱን ያረጋገጠው የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ኃላፊ ሥምና ፊርማ፣

መ) የምስክር ወረቀቱ የሚታደስበት ጊዜ እና

ሠ) ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን

የያዘ መሆን አለበት፡፡

## 21. የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ጊዜ

የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ጊዜ ለአንድ አመት ነው፡፡

## 22. የምስክር ወረቀት ስለማደስ

1) ማንኛውም የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ማብቂያ ቀን በኂላ ካልታደሰ አያገለግልም፡፡

2) የምስክር ወረቀቱ ባለቤት የምስክር ወረቀቱ የአገልግሎት የጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት የእድሳት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

3) የተጠቃሚነት የምስክር ወቀረትን ለማሳደስ ተጠቃሚዎች መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፤

ሀ) ለበጀት ዓመቱ የታደሰ ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የንግድ ፈቃድ፣

ለ) በቀዳሚው ዓመት በተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ተጠቅሞ ባስገባው ጥሬ ዕቃዎች በትክክል ሥራ ላይ የዋሉ ስለመሆናቸው ወይም በመጋዘን የሚገኙ

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት

ስለመሆኑ ከኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ለሚኒስቴሩ የተጻፈ የማረጋገጫ ደብዳቤ

ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 23. የምስክር ወረቀት ስለሚታገድበት ሁኔታ

ጉዳዩ በሚመለከተው ሦስተኛ ወገን አመልካችነት ወይም በሚኒስቴሩ ወይም በምስክር ወረቀት ሰጪው አካል አነሳሽነት የምስክር ወረቀት ያለአግባብ ስለመሰጠቱ ሲደረስበትና የምስክር ወረቀቱ ካልታገደ በቀር ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ ሲረጋገጥ በሚኒስቴሩ ወይም በምስክር ወረቀት ሰጪው አካል በምስክር ወረቀቱ ላይ ጊዜያዊ የእግድ ትዕዛዝ ሊያስተላለፍ ይችላል፡፡

## 24. የምስክር ወረቀት ስለሚሰረዝበትና በድጋሚ ስለሚወሰድበት ሁኔታ

1) የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ የምስክር ወረቀት ሊሰርዝ ይችላል፤

ሀ) አንድ ድርጅት የምስክር ወረቀት የወሰደበትን ሥራ የተወ እንደሆነ የጉምሩክ ኮሚሽን ክሊራንስ ሲያቀርብ፣

ለ) የምስክር ወረቀት የወሰደው ድርጅት የምስክር ወረቀቱ እንዲሰረዝለት ሲጠይቅ የጉምሩክ ኮሚሽን ክሊራንስ ሲያቀርብ፣

ሐ) ድርጅቱ የምስክር ወረቀት የወሰደው ሀሰተኛ መረጃ ወይም ሰነድ አቅርቦ ከሆነ፣

መ) የወሰደው የምስክር ወረቀት ካላሳደሰ፣

ሠ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠው ድርጅት የመመሪያውን መስፈርቶች ሳያሟላ ሲቀር ፤

እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

2) የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 መሠረት የምስክር ወረቀቱን ከመሰረዙ በፊት ድርጅቱ የመቃወሚያ ሐሳብ ካለው እንዲያቀርብ ባስመዘገበው አድራሻው በደብዳቤ ማሳወቅ አለበት፣

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት

3) ድርጅቱ ደብዳቤው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የመቃወሚያ ሀሳብ ካላቀረበ ወይም ያቀረበው የመቃወሚያ ሀሳብ የሕግ መሠረት የሌለው ከሆነ ወይም ባስመዘገበው አድራሻ ሊገኝ ካልቻለ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 25. የአገልግሎት ክፍያ

ማንኛውም ተጠቃሚ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ወይም ለማሳደስ ለሚያገኘው አገልግሎት የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

### 26. ቅሬታ ስለማቅረብ

1) በዚህ መመሪያ በሚሸፈን በማናቸውም ጉዳይ ቅሬታ ያለው ተጠቃሚ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ሦስተኛ ወገን ቅሬታ የሚያቀርብበት ጉዳይ ውሳኔ ባገኘ በ10 ቀናት ውስጥ ለምስክር ወረቀት ሰጪው አካል የቅሬታ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፣
2) የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል የቀረበውን አቤቱታ ሰምቶ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለተጠቃሚው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ሆኖም በተጠቀሱት ቀናት ውስጥ የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ውሳኔውን ያላሳወቀው እንደሆነ ቅሬታ አቅራቢው ለሚኒስቴሩ የበላይ አመራር አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ የበላይ አመራሩ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠው ቅሬታ አቅራቢው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፣
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የበላይ አመራሩ በሰጠው ውሳኔ ላይ በሕግ ጉዳይ ረገድ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታ ያቀረበበት ጉዳይ ውሳኔ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

### 27. መሸጋገሪያ ድንጋጌ

የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓትን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 542/2013 የተጀመሩ ጉዳዮች በዚሁ መመሪያ ቁጥር 542/2013 መሠረት እንዲጠናቀቁ መደረግ አለበት፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry Archives
መዝገብ ቤት

## 28. የተሻሩ መመሪያዎች

1) የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓትን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 542/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።
2) ሌሎች ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ መመሪያዎች ካሉ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

## 29. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በሚኒስቴሩ ሊሻሻል ይችላል።

## 30. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ጸድቆ፣ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ እና በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ ሚያዝያ፣ 2017ዓ.ም

መላኩ አለበል

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry Archives
መዝገብ ቤት

# ቅጾች

## ቅጽ አንድ "ሀ"
## የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ቀጥተኛ አምራች ላኪዎች የሚገቡት የግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት ____________________ በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር ______ በ ________ ____________ የሥራ መስክ የተሠማራሁ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት ከዚህ ጋር አያይዤ ያቀረብኳቸውን ለወጪ ምርቶች ግብዓትነት የምጠቀምባቸውን የውጭ ጥሬ ዕቃዎችንና አላቂ የምርት መገልገያዎችን ከቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነው ለማስገባት እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኩት አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ በተመለከቱት ቅጾች እና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ፡፡

1. የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ወይም የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ወይም የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ አለመሆኔን፣
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሚያደርገው ሥራና ክትትል አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ለማድረግ፣
3. ያቀረብኩት የጥሬ ዕቃ እና አላቂ የምርት መገልገያ ዓይነት ኤክስፖርት ለማደርጋቸው ምርቶች የሚያስፈልጉት ብቻ መሆናቸው፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርት በማምረት ወደ ውጭ የምልክ መሆኑን፣
4. ያቀረብኩት የግብዓት ምርት ጥመርታ አንድን የወጪ ምርት ለማምረት በሚያስፈልገው መጠን መሠረት መሆኑን፣(እንደአስፈላጊነቱ)፣
5. የቫውቸር ሥርዓትን በመጠቀም በኩል በአዋጁ የተደነገጉትን እና በመመሪያው የተቀመጡትን ግዴታዎች ሁሉ ላሟላ፣ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ፡፡

የአመልካች ስም ______________________________________

ፆታ ____________

የድርጅቱ ስም ________________________________________

ማመልከቻው የቀረበበት ቀን ________________

የአባሪ ገጽ ብዛት _________

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry Archives
መዝገብ ቤት

ፊርማ ____________

የድርጅቱ ማህተም ____________________

**<u>ቅጽ አንድ "ለ"</u>**

**<u>የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች የሚገቡት ግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ</u>**

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት ________________________በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር _______ በ _______ __________የሥራ መስክ የተሰማራሁ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት ከዚህ ጋር አያይዤ ያቀረብኳቸውን ያለቀላቸው የወጪ ምርቶች ወይም ለወጪ ምርቶች በግብዓትነት የሚውሉ በከፊል የተዘጋጁ ምርቶች ወይም ጥሬ ዕቃውን ባለበት ሁኔታ ለላኪ፣ ለአምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ላልሆነ አምራች ላኪ ለማቅረብ የምጠቀምባቸውን የውጭ ጥሬ ዕቃዎችና አላቂ የምርት መገልገያዎች ከቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነው ለማስገባት እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኩት አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ በተመለከቱት ቅጾችና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ፡፡

ማረጋገጫ፡-

1. የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ወይም በቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ወይም የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት ሥርዓት ተጠቃሚ አለመሆኔን፣
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሚያደርገው ሥራና ክትትል አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ለማድረግ፣
3. ያቀረብኩት የጥሬ ዕቃ እና አላቂ የምርት መገልገያ ዓይነትና መጠን ለላኪው ለማቀርባቸው ምርቶች ማምረቻ የሚያስፈልጉት ብቻ መሆናቸው፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርት በማምረት ቀጥተኛ ለሆነው ላኪ የማስረክብ መሆኑን፣
4. ያቀረብኩት የግብዓት ምርት ጥመርታ አንድን ለላኪው የሚቀርብ ምርት ለማምረት በሚያስፈልገው ጥሬ ዕቃ መጠን መሠረት መሆኑን፣(እንደአስፈላጊነቱ)፣
5. ምርቶቹን ለላኪው ሳቀርብ በአገር ውስጥ በምርቶቹ ላይ ሊከፈል የሚችል ወይንም የተከፈለ የቀረጥ መጠን ለመግለጽ፣
6. የቫውቸር ሥርዓትን በመቀጠም በኩል በአዋጁ የተደነገጉትን ግዴታዎች ሁሉ ላሟላ፣ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ፡፡

የአመልካች ስም ________________________________

ጾታ ___________

የድርጅቱ ስም ______________________________________

ማመልከቻው የቀረበበት ቀን ________________

የአባሪ ገጽ ብዛት________________

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት

ፊርማ ________________

የድርጅቱ ማህተም ______________________________

## ቅጽ አንድ "ሐ"

## የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች የሚገቡት ግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት __________________በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር _____ በ _______ __________የሥራ መስክ የተሠማራሁ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት ከዚህ ጋር አያይዤ ያቀረብኳቸውን ለወጪ ምርቶች በግብዓትነት የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች ባሉበት ሁኔታ ለላኪ፣ ለአምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ላልሆነ አምራች ላኪ ለማቅረብ የምጠቀምባቸውን የውጭ ጥሬ ዕቃዎችና አላቂ ከቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነው ለማስገባት እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኩት አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ በተመለከቱት ቅጾች እና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ፡፡

1. የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ወይም የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ወይም የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ አለመሆኔን፣
2 የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሚያደርገው ሥራና ክትትል አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ለማድረግ፣
3 ያቀረብኩት የጥሬ ዕቃ እና አላቂ የምርት መገልገያ ዓይነትና መጠን ለላኪው ለማቀርባቸው ምርቶች ማምረቻ የሚያስፈልጉት ብቻ መሆናቸው፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርት በማምረት ቀጥተኛ ለሆነው ላኪ የማስረክብ መሆኑን፣
4 ያቀረብኩት የግብዓት ምርት ጥመርታ አንድን ለላኪው የሚቀርብ ምርት ለማምረት በሚያስፈልገው ጥሬ ዕቃ መጠን መሠረት መሆኑን፣(እንደአስፈላጊነቱ)፣
5 ምርቶቹን ለላኪው ሳቀርብ በአገር ውስጥ በምርቶቹ ላይ ሊከፈል የሚችል ወይንም የተከፈለ የቀረጥ መጠን ለመግለጽ፣
6 የቫውቸር ሥርዓትን በመጠቀም በኩል በአዋጁ የተደነገጉትን እና በመመሪያው የተቀመጡትን ግዴታዎች ሁሉ ላሟላ፣ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ፡፡

የአመልካች ስም ______________________________________

ፊርማ ___________

የድርጅቱ ስም ______________________________________

ማመልከቻው የቀረበበት ቀን ________________

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት
Ministry Of Industry Archives

የአባሪ ገጽ ብዛት ________
ፊርማ ___________
የድርጅቱ ማህተም __________________

## ቅጽ አንድ "መ"

## የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት እና የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚዎች የሚገቡት ግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ ወ/ት ______________________________በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር __________ ______________ በ ________________________________የሥራ መስክ የተሠማራሁ ሲሆን የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት ሙሉ በሙሉ ወደ ውጭ የምልካቸውን ምርቶች ለማምረት የምጠቀምባቸውን ጥሬ ዕቃዎች ከቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነው ለማስገባት እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኩት አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ በተመለከቱት ቅጾችና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት ፈቃድ ለማግኘት እንድችል አመለክታለሁ፡፡

ማረጋገጫ፡–

1. የማመርታቸውን ምርቶች ሙሉ በሙሉ ወደ ውጭ የምልክ መሆኔን፣
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሚያደርገው ሥራና ክትትል አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ላደርግ፣
3. የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ አለመሆኔን፣
4. ከውጭ የማስገባቸው ጥሬ ዕቃዎች ኤክስፖርት ለማደርጋቸው ምርቶች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ብቻ መሆናቸውንና በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርት በማምረት ወደ ውጭ የምልክ መሆኑን እንዲሁም ለምርቱ የሚያስፈልግ መጠን የሚያመለክት የግብዓት ምርት ጥመርታውን ምርቱ በተላከ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በማቅረብ የማጸድቅ መሆኔንና አዲስ የወጪ ምርት ወይንም ግብዓት ለኤክስፖርት ተግባር ከዋለ ይህንኑ በየጊዜው ለማቅረብ፣(እንደአስፈላጊነቱ)፣
5. ሥርዓቱን በመጠቀም በኩል በአዋጁና መመሪያዎች የተደነገጉትን ግዴታዎች ሁሉ ላሟላ፣ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ፡፡

የአመልካች ስም ______________________________
ፊርማ ____________________
የድርጅቱ ስም _______________________________
ማመልከቻው የቀረበበት ቀን __________________

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት

የአባሪ ገጽ ብዛት__________

ፊርማ____________

የድርጅቱ ማህተም ________________

## ቅጽ አንድ "ሠ"
## የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚዎች የሚገቡት ግዴታና የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ ወ/ት ______________________________በግብር ከፋይ ቁጥር -----------በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር _____________ በ ______________________ የሥራ መስክ የተሰማራሁ ሲሆን በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት በዋናነት ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ጊዜ ወደ ውጭ የሚልኩ ድርጅቶች ምርት ለማምረት የሚጠቀሙባቸውን ጥሬ ዕቃዎችን፣ አክሰሰሪዎችና ኮምፓነንቶች ከቀረጥ ክፍያ ነፃ ሆነው በማስገባት ለማቅረብ እንድችል ከዚህ በታች በሰጠሁት ማረጋገጫና ከዚህ ማመልከቻ ጋር አያይዤ ባቀረብኩት አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ በተመለከቱት ቅጾችና በተያያዙት ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች መሠረት ፈቃድ ለማግኘት እንድችል አመለክታለሁ፡፡

ማረጋገጫ፡–

1. በብዛት የሚፈለጉ፣ ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ያሟሉና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ለማቅረብና ለዚህም በቂ ክምችት ለመያዝ፣
2. የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚፈጥሩ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ለመስጠት እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ጥሬ ዕቃዎችን ከአገር አስወጥቼ ለማስወገድ፣
3. ኬሚካልና ዳይስታፍ የማቀርብ ከሆነ እውቅና ካለው ላቦራቶሪ የኬሚካሎቹን የፍተሻ ውጤት የሚገልጽ ሰርቲፊኬት ለማቅረብ፣
4. በሂደት ጥሬ ዕቃዎችን ወይንም ኮምፖኔንቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት ይህንንም በቀጣይ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለመጀመር፣
5. ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ህጎችን ላሟላ፣
6. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሚያደርገው ሥራና ክትትል አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ላደርግ፣
7. ሥርዓቱን በመጠቀም በኩል በአዋጁና መመሪያዎች የተደነገጉትን ግዴታዎች ሁሉ ላሟላ፣

ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ፡፡

የአመልካች ስም ______________________________

ፊርማ ____________

የድርጅቱ ስም ____________________________

ማመልከቻው የቀረበበት ቀን _______________

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት
Ministry Of Industry Archives

የአባሪ ገጽ ብዛት__________

ፊርማ __________________

የድርጅቱ ማህተም ______________________________________

**ቅጽ ሁለት "ሀ "**

**የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ድርጅቱ አጠቃላይ መግለጫ**

1. የድርጅቱ ስም ____________________________
2. የድርጅቱ ሙሉ አድራሻ
   ክልል_______ ዞን/ክፍለ ከተማ__________ ወረዳ_______
   ቀበሌ_________ የቤት ቁጥር________ስልክ ቁጥር _________________
3. የድርጅቱ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ________________
4. ድርጅቱ የተቋቋመበት ዘመን ____________________________
5. ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ያለው የካፒታል መጠን ________
   ሀ/ ቋሚ የማምረቻ መሣሪያዎች ብር _______________________
   ለ/ ሕንፃ ብር ____________________________________
   ሐ/ የሥራ ማስኬጃ ብር _____________________________
   መ/ ሌሎች ብር ____________________________
   ድምር _________________________
6. የድርጅቱ የተጣራ ሀብት ብር _______________
7. የድርጅቱ ሠራተኛ ብዛት ________________________________
   ሀ/ ቋሚ የፋብሪካ ሠራተኛ ወንድ __________ ሴት ________
   ለ/ ጊዜያዊ የፋብሪካ ሠራተኛ ወንድ _________ ሴት ________
   ሐ/ ሌሎች ሠራተኞች ወንድ _________ ሴት ________
8. ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ያለው የይዞታ ሁኔታ፣
   ሀ/ የግል ☐
   ለ/ የጋራ ☐
   ሐ) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ☐
   መ/ የጋራ ማህበር ☐
   ሠ/ የመንግሥት ☐
9. ድርጅቱ ቀጥተኛ ባልሆነ ወይም በቀጥታ ያገኘው የሁለት ዓመት የኤክስፖርት የሽያጭ
   ሀ) በቀጥታ ለውጪ ገበያ በማቅረብ በአሜሪካን ዶላር _______________
   ለ) ወደ ውጭ ለሚልኩት በማቅረብ በብር___________________
   የድርጅቱ ባለቤት ስም ______________________
   ፊርማ _________________

ማህተም______________________

የኢ... ሚኒስቴር መዝገብ ቤት
Ministry Of Industry Archives

## ቅጽ ሦስት

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

## የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት
## CERTIFICATE FOR EXPORT DUTY INCENTIVE SCHEME ENTITLEMENT

የምስክር ወረቀቱ ቁጥር
Certificate No.---------------------------

የተሰጠበት ቀን
Date of Issue ------------

-----------

በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 768/2004 መሠረት ይህ የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል።

This Certificate for Export Duty Incentive Scheme Entitlement is issued pursuant to the Export Duty Incentive Proclamation No. 768/2004.

የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻው ሥርዓት ዓይነት ----------------------------------------

Type of Export Duty Incentive Scheme

የድርጅቱ/የድርጅቱ ባለቤት ስም ----------------------------------------

Name of the Owner/or the Undertaking

የስራ አስኪያጅ ስም ----------------------------------------------------------------------------

Managers Name

ዜግነት ------------------------------------------------------------------

Nationality

የባለቤቱ አድራሻ፣ ክልል ------- ከተማ ------- ወረዳ ----ቀበሌ ------ የቤት ቁጥር-----ስልክ------

-- Address of the Owner:- Region --------City--------Wereda--------Kebele--------House No. --------Phone----------
----------

የድርጅቱ የሥራ መስክ ----------------------------------------

Activities of the Undertaking

የድርጅቱ አድራሻ: ክልል ------ ወረዳ/ከተማ ------- የቤት ቁጥር _____ ስልክ------------
--

Address of the Undertaking:- Region---------Wereda/City----------House No. ------------- Phone--------
-------------

የኃላፊ ስምና ፊርማ ----------------------
Name and Signature of the official

ዕድሣት/Renewal



...ንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ከ -------- እስከ -------ታድሷል፡፡<br>Renewed from To<br>ፊርማ ----------------<br>Signature<br>ስም ----------------<br>Name<br>ማህተም/Seal | ከ ----------- እስከ --------ታድሷል፡፡<br>Renewed from To<br>ፊርማ ----------<br>Signature<br>ስም ----------<br>Name<br>ማህተም/Seal | ከ --------- እስከ --------ታድሷል፡፡<br>Renewed from To<br>ፊርማ ----------<br>Signature<br>ስም ----------<br>Name<br>ማህተም/Seal | ከ --------- እስከ ---------ታድሷል፡፡<br>Renewed from To<br>ፊርማ ----------<br>Signature<br>ስም ----------<br>Name<br>ማህተም/Seal |

## ማሳሰቢያ/Notice:

1. ይህ የምስክር ወረቀት የድርጅቱ ባለቤት "በቅጽ አንድ" ባቀረቡት የማመልከቻ ፎርም በሰጡት ማረጋገጫና በተስማሙት መሠረት የተሰጠ ነው፡፡
   This Special Certificate is issued to the owner of the undertaking based on his/her declaration specified under "Annex 1" of his/her application form.

2. የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ለአንድ ዓመት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡ ስለዚህም የምስክር ወረቀቱ የመጠናቀቂያ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት መታደስ አለበት፡፡

This certifiacate is valid for a period of one year. It is therefore, necessary to renew the certificate before the expiry of its validity.

## የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት ግዴታዎች

- ለቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት በቀረበው ቅጽ መሠረት በአመልካቹ ተሞልቶና በፊርማው ተረጋግጦ የቀረበ ግዴታ የተገባበት ማረጋገጫ፣ የድርጅቱን አጠቃላይ መግለጫ እና ስታንዳርድ ላልወጣላቸው የኤክስፖርት ምርቶች የግብኣት ምርት ጥምርታ መቅረብ አለበት፣
- ለበጀት ዓመቱ የታደሰ የአምራችነት ንግድ ፈቃድ ወይም ድርጅቱ በፕሮጀክት ደረጃ ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣
- የምስክር ወረቀቱ በተሰጠ ወይንም በታደሰ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ድርጅቱ ጉምሩክ ኮሚሽን ቀርቦ አስፈላጊው ስርዓት ማከናወን አለበት፣
- የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚነት ልዩ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ወይም ከታደሰበት ጊዜ ጀምሮ **ለአንድ ዓመት ብቻ** ያገለግላል፣
- የጉምሩክ ኮሚሽን የጥሬ ዕቃውን ባህሪ መሠረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፣
- የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚ ጊዜ ገደቡ ከማለፉ ከአንድ ወር በፊት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፣



የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት
Ministry Of Industry Archives

- የመጠቀሚያው የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ወይም በአዋጅ ቁጥር 768/2012 አንቀጽ 25 መሠረት ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በአገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባልዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና በተጨማሪም የቀረጡን ሂሳብ **50 በመቶ** እንዲከፍል ይደረጋል፣
- የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ ለሚኒስቴሩ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ ባለፈው ዓመት ለኤክስፖርት ምርቱ እንዲውል በሥርዓቶቹ አማካኝነት ከቀረጥ ነፃ ሆነው ከውጪ አገር የገቡ ጥሬ ዕቃዎች በትክክል ሥራ ላይ ያዋሉ ስለመሆናቸው ወይም በመጋዘን የሚገኙ ለመሆኑ ጉምሩክ ኮሚሽን ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው፣

## <u>ቅጽ አራት</u>

## <u>የኢንዱስትሪ ቀጠና አመልካች ድርጅቶች የሚያቀርቡት ማመልከቻ</u>

1. የአመልካች ስም፤-----------------------------------------------------
2. የሥራ ድርሻ፤-------------------------------------------------
3. አድራሻ

   የባለቤቱ አድራሻ፡- ክልል----------------------- ከተማ------------------ወረዳ---------------

   ቀበሌ------------------ የቤት ቁጥር -------------------- ስልክ---------------

   የድርጅቱ አድራሻ፡- ክልል----------------------- ከተማ------------------ወረዳ-------------

   ቀበሌ------------------ የቤት ቁጥር -------------------- ስልክ---------------
4. የታክስ መለያ ቁጥር፤----------------------------------
5. ዜግነት፤-------------------------
6. የንግድ ስም፤ -----------------------------------
7. የንግድ ፈቃድ ቁጥር፤------------------ የንግድ ፈቃድ የወጣበት ቀን፤ -----------------
8. የድርጅቱ ህጋዊ አቋም (ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ፣ ብቸኛ ባለቤት ወዘተ)፤

   -------------------------------------------------------------------------------------.
9. መግባት የሚፈልግበት የኢንዱስትሪ ቀጠና ስም፤ -----------------------------------------

   ---------------------------------------.



የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት

10. ሊከናወን የታሰበው የአምራች ዘርፍ ኢንቨስትመንት ሥራ አጭር መግለጫ፤------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------.

11. ኢላማ የተደረጉ ገበያዎች /ገዢዎች፤ ---------------------------------------------------.

12. የሚመረቱ ምርቶች አይነት፤-----------------------------------------------------.

13. ማመልከቻ በቀረበበት የአምራች ዘርፍ ያለ ልምድ መጠን፤ ------------------------------.

14. ምርትን ወደ ውጭ የሚልክ ድርጅት ከሆነ የሚላኩት ምርቶች መጠን እና የሚገኝ የገንዘብ መጠን ግምት፤ ------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------.

15. አቅራቢ ድርጅት ከሆነ ለኢንዱስትሪ ቀጠና ባለሀብቶች የሚቀርብ ምርት አይነትና መጠን፤ ---------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------.

16. አሁን ያሉ ሰራተኞች ብዛት፤--------------------.

16.1 ወደፊት በኢንዱስትሪ ቀጠና ስራ ሲጀመር የሚቀጠሩ ሠራተኞች ብዛት፤--------

---------------------------------------------------------------------------.

17. አመልካች ድርጅቱ ለምርትና የተለያዩ ተግባራት የሚያስፈልገው የሼድ/መሬት መጠን፤-----------------------------------------------------------------------------------.

18. የሼድ ቦታ/የለማ መሬት ከተሰጠ በኋላ የምርት ስራ ለመጀመር የሚያስፈልገው ጊዜ ግምት፤ ----------------------------------------------------------------------.

19. ለተመለከተው ስራ የሚያስፈልገው ካፒታል አጠቃላይ መጠን፤በአሃዝ-------------------

/ በፊደል -----------------------------------------------

19.1 በድርጅቱ የሚቀርብ ካፒታል ድርሻ መጠን፤ በአሃዝ -----------------------

/በፊደል----------------------------------------------------



Ministry Of Industry Archives
መዝገብ ቤት

19.2 የታቀደው ካፒታል ምንጭ፤ በአሃዝ -------------------------------/በፊደል------------------------------------------------

19.3 የዓመታዊ ሽያጭ ገቢ ግምት (በአሜሪካ ዶላር ወይም በብር)፤

በአሃዝ ------------------------------/ በፊደል-------------------------------------------------.

20. ድርጅቱ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን የመሰረተ ልማት (የሀይል አቅርቦት ፣ የውሃ ፣ የደረቅ እና የፈሳሽ ቆሻሻ መጠን ፣ የቴሌኮም አገልግሎት) አቅርቦት ጥያቄ በዝርዝር

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Industry
Archives
መዝገብ ቤት